የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
JARAA'IDKA FEDERAALKA OGAYSIISYADA EE JAMHUURIYADA DIMUQRAADIGA FADERALKA ITOOBIYA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፮
አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

Waxaa soo saaray Golaha Wakiilada shacabka Jamhuuriyadda Dimuqraadiga Federaalka Itoobiya

SANADKII 26AAD TIR. 76
ADDIS ABABA 25TH AUGUST 2020

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፫/፪ሺ፲፪ ዓ.ም
የማህበረሰብ ተፋሰሶች፣ ልማት፣ አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ..........................................ገጽ ፲፪ሺ፯፻፴፫

Qaybaha

Bayaan Tir.1223/2020
Bayaanka Horumarinta, Maaraynta Iyo Isticmaalka Biyo-Rogyada…. Bog 12,733

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፫/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

## የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት፣ አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ

የአካባቢ መራቆትንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን በመከላከል፣ የብዝሀ ሕይወት ሀብትን በመጠበቅ፣የውኃ ሀብትን በማጎልበትና የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት በመቀነስ የመሬት የማምረት አቅም ተጠብቆ ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፍ እና በዚህም ለሰብልና ለእንስሳት ሃብት ልማት ሥራ ምቹ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፤

የአርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ እና ከፊል አርብቶ አደሩ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር በማድረግ ለምግብ ዋስትና መረጋገጥና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ምቹ መደላድል ለመፍጠር ይቻል ዘንድ ቀደም ሲል የተጀመሩትን የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ማስቀጠል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ባለፉት ዓመታት የተከናወኑት የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ከፍተኛ የሰው ጉልበትና የገንዘብ ወጪ ተደርጐባቸው እንዲለሙ የተደረገ ቢሆንም ዘላቂነታቸውን ለማረጋገጥ የተፋሰሱ ተጠቃሚዎች በባለቤትነት ስሜት ተረክበው የተፈጥሮ ሀብቶችን የሚያስተዳድሩበት የርክክብ፣ የአጠቃቀም፣ የአጠባበቅና የተጠያቂነት አሠራር ማስፈን ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

## BAYAAN TIR. 1223/2020

Bayaanka horumarinta, maaraynta iyo isticmaa biyo-rogyada.

MAADAAMA, ay lagamamaarmaan tahay in laga hortago xaalufka deegaanka iyo hoos u dhaca khayraadka dabiiciga ah, iyo dhowrida noolaha kala duwan, sidoo kalena la horumariyo kharyaadka biyaha loona yareeyo dikhowga hawada, si loo joogteeyo wax soosaarka dhulku u leeyahay dadka dhalan doona kuna haboon horumarinta midhaha iyo xoolaha;

MAADAAMA, ay lagamamaarmaan tahay si loo balaadhiyo shaqooyinka horumarinta biyorogyada iyadoo looga jeedo kor u qaadida wax tarka iyo wax soosaarka beeralayda, reer guuraaga iyo xoolo dhaqato-beeralayda si loo xaqiijiyo damaanadda cuntada loona abuuro xaalad dagan oo saamaxda fursado;

MAADAAMA, Inkastoo la qabtay shaqooyin ku saabsan hourmarinta biyorogyada sanadihii lasoo dhaafay iyadoo la galiyey khayraad dad iyo lacageed oo badan, xaqiijinta in ay waartaa ay baahan tahay in dib loo habeeyo oo isticmaalayaasha biyoroggu qaataan masuuliyada maarayneed, isticmaal iyo ilaalinta khayraadka dabiiciga ah si lahaansho leh;

የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ያለሙትን ሀብት ለማስተዳደር፣ ለመጠቀምና ለመጠበቅ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚችሉበትን ሁለንተናዊ አቅም ማሳደግ በማስፈለጉ።

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፪/ (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የማህበረሰብ ተፋሰሶች፣ ልማት፣ አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፫/፪ሺ፲፪ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ “የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ሕብረት ሥራ ማኅበር” ማለት ሰዎች የማህበረሰብ ተፋሰስን ለማልማት ፣ ለመጠበቅና ለመጠቀም በፈቃደኝነት የሚያቋቋሙት በጋራ ባለቤትነት የሚያስተዳድሩት፣ በህብረት ሥራ መርህ መሠረት የሚመሩትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚመራ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ማህበር ነው፤

፪/ “የማህበረሰብ ተፋሰስ” ማለት ወደ አንድ መልክዓ-ምድራዊ አቅጣጫ የሚፈስሱ የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውኃዎች የሚያካልሉትን አካባቢ የሚያካትት፣ አነስተኛ ተፋሰስ ሆኖ አማካይ ስፋቱ ከ ፭፻ ሄክታር የማይበልጥ የመሬት ክፍል ነው፤

፫/ “የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት” ማለት በማህበረሰብ ተፋሰሱ ክልል ውስጥ የሚገኘውን የአፈር፣ የውሃ እና የዕጽዋት ሀብት ለመጠበቅና ምርታማነቱን ለማሳደግ የሚረዱ ተግባራትን አቀናጅቶና አጣጥሞ ማከናወን ማለት ነው፤

MAADAAMA, ay lagamamaarmaan tahay inla kubciyo awooda guud ee bulshada isticmaasha biyo rogyada si ay u maareeyaan, u isticmaalaan una ilaaliyaan kharaadka dabiiciga ee ay wax ka qabsadeen si ay u xaqiijiyaan iticmaalkooda dhaqaale bulsho .

HADABA, SIDAA DARAADEED, Sida ku cad Qodobka 55 (1) iyo (2)(a) ee dasduurka dawlada dimuqraadiga fedaraalka ee Itoobiya, waxaa la xeershay sidan soo socota:

## QAYBTA 1aad

## TIBXAHA GUUD

### 1. Magaca gaaban

Bayaankan waxaa loo tixraaci karaa “Bayaanka horumarinta, maaraynta iyo isticmaalka biyo rogyada Tir. 1223/2020”

### 2. Qeexid

Bayaanka, hadaan xaalad kale badalin:

1/ “Iskaashatooyinka bulshada ee isticmaala biyo-roga” micnaheedu waa urur ku aas aasmay danta guud ee bulshada /biyo-rog isticmaalayaasha yaryar oo ku salaysan qawaaniin iskaashato bulsho oo ay ku jirto in isticmaalayaashu maareeyaan, ilaaliyaan ugana faa’ idaystaan biyo-rogyada si dimuqraadi ah;

2/ “Bulsho/Biyo-rog yar” waa aag juquraafi haaneed oo ay xadiday xuduudda biyo-rogga oo ay ku jiraan biyaha oogada iyo kuwa dhulkuba ee u wada socda jiho siman oo xajmigeeduna yahay celecelis ahaan qiyaastii 500 hektar;

3/ ‘’Horumarinta biyo-rogga bulshadu’’ waa talaabooyin lagu midaynayo isticmaalka carada,biyahah iyo doogga si loo ilaaliyo khayraadkaas loona badiyo wax soosaarka biyo-rogga bulshada;

፬/ “የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች” ማለት በማህበር ተደራጅተውም ይሁን ሳይደራጁ ተፋሰሱ በመልማቱ ምክንያት የሚፈጠረውን ሀብት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጠቀሙ የህብረተሰብ ክፍሎች ማለት ነው፤

4/ “Bulshada ah Isticmaalayaasha Biyo-rogga” Waa shakhsiyaad si toos ah ama si dadban uga fa’iidaysta khayraadka la horumariyey ee biyo-rogga iyagoo ah shakhsi ama urur loo sameyey ka fa’iidaysigan;

፭/ “የወል ይዞታ” ማለት በተጠቃሚዎች ስምምነት በሚተዳደር ተፋሰስ ውስጥ በግል፣ በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ያልተያዙ ይዞታዎች እና የአካባቢው ነዋሪዎች በጋራ ይዞታነት የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት ሥራዎች በመሥራት አልምተው እንዲጠቀሙበት በመንግሥት የተሰጣቸው የገጠር መሬት ነው፤

5/ “Dan guud/Dhul day ah” waa dhul baadiye ah oo ku yaala biyo-rogga dhexdiisa ayna maaraystaan isticmaalayaashiisa halkaasi oo aan loo lahayn si shakhsi ah, Dawli ah, haayad ama xafiistoona oo ay dawladu ku wareejisay bulshada deegaanka si ay uwada lahaadaan una wada isticmaalaaan iyagoo kana qabanaya ilaalinta khayraadka dabiiciga ah iyo howlaha horumarineed.

፮/ “የግል ይዞታ” ማለት በአርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ወይም በሌሎች በሕግ መብት በተሰጣቸው ሰዎች የተያዘ መሬት ነው፤

6/ “Dhul gaar loo leyahay" waa dhulka ay haystaan xoolo-dhaqato beeralaydu, reer guuraagu ama cid kale oo sharci u siiyey in ay isticmaalaan dhulkaa;

፯/ “የመንግስት ይዞታ” ማለት በፌደራል ወይም በክልል መንግስት ተከልሎ የተያዘና ወደፊት የሚከለለውን መሬት የሚገልፅ ሲሆን የደን መሬቶችን፣ የዱር እንስሳት ጥብቅ ቦታዎችን ፣የመንግስት እርሻዎችን፣ የማዕድን መሬቶችን ሃይቆችን፣ ወንዞችንና በተመሳሳይ መልኩ የተያዙትን ያጠቃልላል፤

7/ "Dhul dawlo" waa dhul xadaysan ama mustaqbalka loo xadayn doono lahaanshaha dawlada federaalka ama ta deegaanada;
Oo ay ku jiraan Kaymaha, Dhulka Duurjoogta Lagu Ilaaliyo, Beeraha Dawladda, Dhulka Macdanta, Harooyinka,Wabiyada Iyo Dhulal Kale;

፰/ “ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች” ማለት በማህበራዊ፣ በጤና ወይም በኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ምክንያት መብታቸውን ለመጠየቅና ለማግኘት ችግር የሚገጥማቸው እንደ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ሕጻናት እና አረጋውያን የመሳሰሉት የኅብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፤

8/ “Dadka baahiyaha gaarkaa qaba” Waa qayb bulshada ka mid ah oo aan dalban karin aanna ilaashan Karin xuquuqahooda sabab arimo bulsho, caafimaad ama dhaqaale ahaaneed sida haweenka, curyaamiinta, caruurta iyo muwaadiniinta da’da ah.

፱/ “ተሳትፎ” ማለት በውሳኔ ሊነኩ በሚችሉ ሀብቶች ላይ መብት ያላቸው ሰዎች በውሳኔ ሰጪነት ሂደት ውስጥ የመሳተፍ መብት ማለት ነው፤

9/ “Kaqayb qaadasho”Waa xuquuqda in laga qayb-qaato hanaanka dhaqan ama sharci ahaaneed ee go’aan gaadhida saamaynaya khayraadyada.

፲/ “ልዩ መለያ” ማለት አንድን አነስተኛ የማህበረሰብ ተፋሰስ ከሌላው ለይቶ ለማወቅና ከክልል፣ ከዞንና ከወረዳ የአስተዳደር ወሰኖች እንዲሁም ከዋና ተፋሰስ ጋር እንዴት እንደሚተሳሰር ለማመላከት የመልክዓ-ምድር መረጃ ሥርዓት

10/ “Made” Waa calaamad lagu garto biyo-rog yar si looga garto kuwa kale; Waxay cadaynaysaa loolalka iyo dhigaha xuduudada maamul deegaan, gobol iyo dagmo iyo biyo-rogga wayn iyadoo la adeegsanayo GIS iyo dhigaha iyo loolalka.

(ጂ.አይ.ኤስ) እና የቦታዎች መገኛ ውቅሮችን (የጂኦግራፊያዊ ኮርዲኔቶችን) በማቀነባበር የሚሰጥ መለያ ነው፤

፲፩/ "የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ" ማለት የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፭/፪ሺ፱ ነው፤

፲፪/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፫/ "ሚኒስቴር /ሚኒስትር" ማለት የግብርና ሚኒስቴር/ ሚኒስትር ማለት ነው፤

፲፬/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው፤

፲፭/ በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው ለሴት ፆታም ያገለግላል።

፫. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በሀገሪቱ ውስጥ በሚገኙ የማኅበረሰብ ተፋሰሶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፬. **<u>የአዋጁ ዓላማዎች</u>**

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ የአካባቢ መራቆትንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን በመከላከል፣ የብዝሃሕይወት ሀብትን በመጠበቅ የውሃ ሀብትን በማጎልበትና የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት በመቀነስ የማህበረሰቡን ለድርቅ ተጋላጭነት መቀነስና የመቋቋም አቅምን ማሳደግ፤

፪/ ዘላቂነት ያለው የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን በማረጋገጥ የመሬትን የማምረት አቅም ማሳደግ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ማድረግ፣ እንዲሁም ለምግብ ዋስትና መረጋገጥና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

11/ "Bayaanka iskaashatooyinka bulshada" Micnihiisu waa bayaanka iskaashatooyinka bulshada Tir. 985/2016

12/ "Deegaan" Waa xukuumad deegaanka kasta sida uu qeexay Qodobka 47 (1) ee dastuurka jamhuuriyadda demuqraadiga ee federalka Itoobiya oo ay ku jiraan maamul magaalooyinka Addis Ababa City Administration iyo Dire Dawa;

13/ "Wasaarad" ama"Wasiir" Waa wasaarada ama wasiirka beeraha;

14/ "Qof" waa qof dabiici ama sharci ah;

15/ Bayaankan, qeexid kasta oo tibaaxaysa labnimo waa in ay sidoo kale tibaaxdaa dhedignimo.

3. Baaxada isticmaalka

Bayaankan waa in loo isticmaalo biyo-rogyada bulahsda ee laga hello wadanka dhexdiisa.

4. Ujeedooyinka Bayaanka

Ujeedooyinka bayaankani waa kuwan soo socda.

1/ Hoos u dhigida u nuglaanshaha bulshada ee abaaraha iyo kor u qaadida awoodooda u adkaysi iyadoo laga hor tagayo xaalufka bay'adda iyo khayraadka dabiiciga ah, ilaalinta noolayaasha kala duwan, horumarinta khayraadka biyaha iyo hoos u dhigida dikhawga hawada.

2/ Horumarinta wax-soosaarka dhulka; kobcinta wax-tarka iyo wax-soosaarka beerolayda iyo reer guuraaga; Xaqiijinta damaanad qaadka cuntada iyo shaqo abuur iyadoo si aye leh loo ilaaniyo, hurumarinayo loona isticmaalayo biyo rogyada bulshada

፫/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች በባለቤትነት ስሜት የተፈጥሮ ሀብቶችን ለማልማት፣ ለመጠበቅ፣ ለማስተዳደርና ለመጠቀም የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ማስፈን ለዚህም የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎችን ሁለንተናዊ አቅም ማሳደግ፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ተፋሰስ ዕቅድና ልማት

### ፭. የተፋሰስ ዓይነቶች

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት እውቅና የተሰጣቸው ተፋሰሶች የማህበረሰብ ተፋሰስና በወረዳ ደረጃ የሚለይ ዋና ተፋሰስ ናቸው።

፪/ የማንኛውም የማህበረሰብ ወይም ዋና ተፋሰስ ስፋት ወይም መልክዓ-ምድራዊ ወሰን በአንድ ውስን አካባቢ የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብት በአንድነት ለማልማትና ብቃት ባለው መንገድ ለመንከባከብ አመች ወይም ተመጣጣኝ ሆኖ የተከለለ መሆን አለበት።

### ፮. የማህበረሰብ ተፋሰስ

፩/ የማህበረሰብ ተፋሰስ አማካይ ስፋት ፭፻ ሄክታር ሆኖ እንደ አካባቢው መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ወይም የተፋሰስ ልማቱን ዓላማ ግምት ውስጥ በማስገባት መጠኑ ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የማህበረሰብ ተፋሰሱ ከ፭፻ ሄክታር በላይ በሚሆንበት ጊዜ ይህንኑ እንደ አመችነቱ ከፋፍሎ ማልማትና መንከባከብ ይቻላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም በመከፋፈሉ ምክንያት የሚፈጠረው ተፋሰስ ስፋት ከ፪፻ ሄክታር በታች ሊሆን አይችልም።

### ፯. ዋና ተፋሰስ

፩/ ዋና ተፋሰስ የማህበረሰብ ተፋሰሶች ስብስብ ሲሆን ስፋቱ እስከ ፳ሺ ሄክታር ሊደርስ ይችላል።

3/ In la sameeyo nidaam awoodsiiinya isticmaalayaasha biyo-rogyada bulshadu si ay u ilaaliyaan,horumariyaan, maamulaan una isticmaalaan khayraadka dabiiciga ah si dareen lahaanshiyo ku jirto iyadoo laga eegayo dhanka kor u qaadida awooda isticmaalayaasha biyo-rogyada bulshada.

## QAYBTA 2AAD

## QORSHAHA IYO HORUMARINTA BIYO_ROGYADA

### 5. Noocyada biyo-rogyada

1/ Biyo-rogyada lagu aqoonsaday bayaankan iyo biyo-rogyada waawayn ee dagmadu sheegto.

2/ Xajmiga ama xuduuda jiquraafi ahaaneed bulsho kasta ama biyo-rogyada waawayn waa in loo xadeeyaa si dagan ama wada-ogol ah si ay u suurowdo hurumarin isku dhaf ah iyo ilaalin hufan ee dhamaan khayraadyada dabiiciga ah ee ku yaal aagaa.

### 6. Biyo-rog bulsho

1/ Celceliska xajmi ahaan ee biyo-rog bulsho waa in uu noqdaa 500 ha. Haseyeeshee, Xajmiga wuu ka waynaan karaa ama ka yaraan karaa intaa iyadoo lagu salaynayo qaab dhismeedka dhulka ama iyadoo lagu xisaabtamayo ujeedada hurumarinta biyo-rogga.

2/ Hadii xajmiga biyo-rog bulshadu ka waynaado 500 hektar sida lagu cadeeyey fakhrada (1) ee qodobkan, biyo-rogga waxaa laga yaabaa in la qaybsho, si ku haboon ujeedada horumarinta iyo ilaalintiisa.

3/ Si ka duwan sida ku cad fakhrada (2) ee qodobkan, xajmiga biyo-rogga ee samaysmay qaybinta ka dib waa in aanu ka yaraan 200 hektar.

### 7. Biyo-rogyada waawayn

1/ Biyo-rogyada waawayn waa isku ururinta biyo-rogyada bulshada waana in ay koobtaa dhul dhan ilaa 20,000 hektar.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም እንደ አካባቢው መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ወይም ለአስተዳደር አመችነት ሲባል መጠኑ ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል።

፫/ ዋና ተፋሰሶች በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ወንዞችን መነሻ በማድረግ ይለያሉ።

፬/ ከዋና ተፋሰሱ ተለይተው የወጡትን የማህበረሰብ ተፋሰሶች ለማልማት ከላይኛው የተፋሰሱ ክፍል በመጀመር ወደታችኛው በቅደም ተከተል መውረድ ያስፈልጋል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከራስጌ በታች ጎንና ጎን ከሚገኙ የማህበረሰብ ተፋሰሶች በቅድሚያ የሚለማውን የመራቆት ደረጃ፣ የሰው ሀይልና የሀብት አቅርቦት ግምት ውስጥ በማስገባት ሊለሙ የሚገባቸው ተፋሰሶችን የመለየት ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

፰. <u>የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ ዝግጅት</u>

፩/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ ዝግጅት የአሳታፊነት መርሕን የተከተለ መሆን አለበት።

፪/ በሚመለከተው አካል የፀደቀ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት ተግባራዊ በሚሆንባቸው አካባቢዎች የመሬት አጠቃቀም እቅዶች በሚኖሩበት ጊዜ የማህበረሰብ ተፋሰስ እቅዶች እነዚህኑ መነሻ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

፫/ የማህበረሰብ ተፋሰስ የሚያለሙ አካላት በቅድሚያ የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

፬/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት መነሻ ዕቅድ የሚዘጋጀው የህብረት ሥራ ማኅበር ከመቋቋሙ በፊት ሲሆን የህብረት ሥራ ማኅበሩ መሥራች ኮሚቴ የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማኅበሩን ከማደራጀት ጎን ለጎን በሚመለከተው የግብርና ጽ/ቤት በመታገዝ ዕቅዱን ማዘጋጀት አለበት።

2/ Si ka duwan sida ku cad fakhrada (1) ee qodobkan, xajmiga biyo-rogyada waa wayni wuu ka waynaan karaa ama ka yaraan karaa iyadoo lagu salaynayo qaab dhismeedka dhulka si ku haboon maarayntiisa.

3/ Biyo-rogyada waa wayn waa in lagu madeeyaa iyadoo lagu salaynayo dooxooyinka waa way nee dagmada ku yaal.

4/ Si loo hurumariyo biyo-rogyada bulshada eel aga soocay biyo-rogyada waa wayn, waxaa lagama maarmaan ah in lagasoo bilaabo dhanka sare biyo-roga wayn oo loo wadaa hoos si isku xigxigta.

5/ Iyadoon la ismoodsiinayn sida uu qabo fakhrada (4) ee qodobkan, Waa in lagu xisaabtamaa heerka xaaluf, Dadka, iyo helitaanka khayraadka meesha si loo ogaado sida loo kala horumarinayo horumarinta biyo-rogyada bulshada ee ka hooseeya biyo-roga sare.

8. Diyaarinta Qorshaha Biyo-rogyada Bulshada

1/ Diyaarinta qorshaha biyo-rogyadu waa in u uku qotomaa qawaaniinta ka qaybgalka.

2/Meelaha leh qorshe nidaam dhul isticmaal iyo marka ay jirto dhul isticmaal ay ansixisay ciday khusaysay, qorshaha biyo-rogyada bulshadu waan ay ku salaysnaato qorshahaas.

3/ Shakhsiyaadka horumarinaya biyo-rogyada bulshadu waa in marka hore ay diyaariyaan qorshaha biyo-rogyada bulshada

4/ Haddii barbilowga qorshaha biyo-rogyada bulshada la diyaariyey intaan la aas-aasin iskaashatada , gudida aas-aastay iskaashatadu waa in iyagoo taageero ka helaya xafiiska beeraha ay diyaariyaan qorshaha si la siman aas-aasida iskaashatada isticmaalayaasha biyo-rogga.

፭/ በሚዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የሚካተቱ ተግባራት የአካባቢ መራቆትንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን ለመከላከል፣ የውኃ ሀብትን ለማጎልበትና የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት በመቀነስ የመሬትን የማምረት አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው።

፮/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት በሚታቀድበት ጊዜ መላ ተፋሰሱን ለማልማት የሚያስችል ዝግጅት በማድረግ ከፊሉ ለምቶ ከፊሉ ሳይለማ እንዳይቀር ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

፯/ ዋና ተፋሰስ የማህበረሰብ ተፋሰሶች ስብስብ በመሆኑ ለልማት ዕቅዱ ተፈፃሚነት ያመች ዘንድ እንደ አስፈላጊነቱ በማህበረሰብ ተፋሰስ ስፋት መጠን ተከፋፍሎ መዘጋጀት ይኖርበታል።

፰/ በተፈጥሮ የተፋሰስና የአስተዳደር ወሰን ልዩነት በሚያሳይ የማህበረሰብ ተፋሰስ ላይ የሚዘጋጀው ዕቅድ የተፋሰስ ወሰንን ተከትሎ ሲሆን ሁሉንም የተፋሰስ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ያሳተፈ መሆን አለበት።

፱/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ዕቅድ አዘገጃጀት የአካባቢና ማኅበራዊ ዘላቂነት መርሕን የተከተለ መሆን አለበት።

፲/ አንድ የማህበረሰብ ተፋሰስ በካርታ የተደገፈ የተሟላ ከ፭ እስከ ፲ ዓመት የረዥም ጊዜ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል።

፲፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበረሰብ ተፋሰሶች የረጅም ጊዜ ዕቅዳቸውን መሠረት ያደረገ ዓመታዊ ዕቅድ ሊዘጋጅላቸው ይገባል።

5/ Howlaha ku jiridoona qorshaha la diyaarin doonaa waa in ay ahaadaan kuwo awoodsiinaya ka hortaga xaalufka bay’ada, hoos u dhaca khayraadka dabiiciga ah; horumarinta khayraadka biyaha; yaraynta dikhawga hawada si loo horumariyo wax-tarka dhulka.

6/Marka horumarinta biyo-rogga bulshada la qorsheeyo, waa in diyaar galow la sameeyaa si loo fudaydiyo horumarinta dhamaan biyo-rogga lagana qaataa taxadar ku haboon si looga fogaado hurumarinta qayb ka mid ah biyo-roga qaybta kalena la iskaga tago.

7/ Si looga yeelo qorshaha horumarinta biyo-rogga mid toolmoon, qorshaha horumarinta biyo-rogga wayn oo ah biyo shubka biyo-rogyada bulshada, waa in la diyaariyaa, sigaar ah waliba hadii ay suuro gasho iyadoo lagu salaynayo baaxada biyo-rogyada bulshada.

8/ Qorshaha loo diyaarshay biyo-rog bulsho, oo xuduuda dabiiciga ah ee biyo-rogga aanay waafaqsanay xuduuda maamul, waa in la raacaa xuduuda biyo-rogga iyadoo lagala tashanayo dhamaan isticmaalayaasha biyo-roggaa dagan.

9/ Diyaraarinta qorshaha horumarinta biyo-rogu waa in ay ku qotontaan qawaaniinta bulsho iyo bay’ad waarta.

10/ Biyo-rog bulsho waa in uu lahaadaa qorshe isku dhaf ah oo fog 5 ilaa 10 sano oo lagu habeeyey khariirad.

11/ Iyadoon la ismoodsiinayn sida uu qabo fakhrada (9) ee qodobkan, qorshayaal sanadle ah waa in loo diyaarshaa biyo-rogyada bulshada iyadoo lagu salaynayo qorshohooda fog.

፲፪/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ አገራዊ ዋና የተፋሰስ ስትራቴጂክ ዕቅድ ለማዘጋጀት በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የወጣ ዕቅድን መሠረት ማድረግ ይኖርበታል

፲፫/ በማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ማኅበሩ የተዘጋጀው ዕቅድ ከአንድ ወረዳ በላይ ወሰን ተሻጋሪ ከሆነ ዕቅዱ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ወረዳዎች ሁሉ ቀርቦ በወረዳዎቹ ግብርና ጽ/ቤቶች ስምምነት መጽደቅ አለበት፡፡

፲፬/ በየአካባቢው የሚለዩ የማህበረሰብ ተፋሰሶች እና ዋና ተፋሰሶች አገራዊውን የልዩ መለያ አሰጣጥ ሂደት ተከትለው ልዩ መለያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

## ፱. <u>የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት</u>

፩/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ሥራዎች ከላይኛው የተፋሰሱ አካል ተጀምረው ወደታችኛው የተፋሰሱ ክፍል መውረድ አለባቸው።

፪/ ለሚለማው ተፋሰስ ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመምረጥ በአግባቡ መተግበር ያስፈልጋል።

፫/ የማህበረሰብ ተፋሰሶች በተፋሰሱ ተጠቃሚዎች፣ በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በሚቋቋሙ ፕሮጀክቶች ወይም በግለሰቦች ሊለሙ ይችላሉ።

፬/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ በተፈጥሮ ተፋሰስና በአስተዳደር ወሰን መካከል ልዩነት ባለው ቦታ ላይ የሚያርፍ በሆነ ጊዜ ዕቅዱ የሚተገበረው የአስተዳደር ወሰንን በመከተል ይሆናል፡፡

፭/ በተፋሰስ ልማት ሥራዎች ላይ ተባይና በሽታን ለመቆጣጠር የተቀናጁ የመከላከያ ዘዴዎች ይተገበራሉ።

፮/ የማህበረሰብ ተፋሰስ አልሚዎች የሚገለገሉበትን ማናቸውም ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ ወይም መሠል ኬሚካላዊ ግብዓት የሚያገኙት ከመንግሥት ወይም ሕጋዊ ፈቃድ ከተሰጣቸው ድርጅቶች ብቻ ይሆናል።

12/ Qorshaha loo diyaarinayo biyo-rog bulsho oo yar waa in u uku salaysnaadaa qorshaha istaraatijiyadeed ee dooxada bulshadu/ biyo-rog bulsho yari ku yaalo oo ay diyaarisay cidda ku amrani.

13/ Marka qorshaha ay diyaariso iskaashatada hurumarinta biyo-rogga bulshadu oo ka gudba xuduuda in ka badan hal dagmo, qorshaha waa in loo gudbiyaa dagmooyinka ay khusayso ayna ansixiyaan iyagoo kaashanaya xafiisyadooda beeraha.

14/ Boyo-rogyada bulshada iyo biyo-rogyada waayn ee laxaqiijiyo, waa in sumadeeyaa iyadoo la raacayo nidaamka sumadaynta qaranka.

## 9. Horumarinta Biyo-rogyada bulshada

1/ Howlaha horumarinta biyo-rogyada bulshadu waa in ay ka bilaabmaan xaga sare una socdaan xagga hoose ee biyo rogga.

2/ Waa lagama maarmaan in la xusho tiknoolojiyad casri ah oo ku haboon biyo-roga la horumarinayo loona isticmaalo si haboon.

3/ Biyo-rogyada bulshada waxaa laga yaabaa in ay horumariyaan isticmaalayaasha biyo-rogyadu, iyagoo isticmaalaya maraariic ay samaysay dawlada ama hayaaduhu amaba shakhsi.

4/ Marka qorshaha biyo-roga bulshadu ku dhaco meel uu farqi u dhexeeyo xuduuda dabiiciga ah ee biyo-roga iyo ta maamul, fulintooda waxaa loo habayn iyadoo la raacayo xuduuda maamulka.

5/ Howlaha lagu horumarinyo biyo-rogyada, qaabab lagu xakamaynayo cudurada iyo cayayaanka waa in la fuliyaa.

6/ Isticmaalayaasha biyo-rogyada bulshadu waa in ay ka helaan gashiga kasta oo bacarinta dad sameega ah iyo kiimiko kasta kaliya dawlada uun ama cid kale oo shati sharci ah u haysata howshan.

፯/ ማንኛውም ፀረ-ተባይ ኬሚካል ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ ሁሉ በንብ እርባታ፣ በሰብልና በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ኬሚካሉን የሚያሰራጨው ሕጋዊ አካል ለኬሚካሉ ተጠቃሚዎች በቂ ዕውቀት ማስጨበጥና ተገቢውን ወቅትና የአጠቃቀም ጊዜ መርጠው ርጭቱን እንዲያካሂዱ ማድረግ ይኖርበታል። ለንብ አርቢዎችም ርጭቱ ከመደረጉ በፊት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተግባራት መፈፀም አለባቸው፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንዳንድ ኬሚካሎች ካላቸው ጠንካራ መርዛማነት የተነሳ በዕፅዋትና በአካባቢው ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ በባለሙያ ድጋፍ እንዲረጩ ወይም በእርሱ የቅርብ ክትትል ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረግና የቅሪቶች አወጋገድ የአካባቢ ጥበቃ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

፱/ በማህበረሰብ ተፋሰሱ ክልል ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብዓቶች ደረጃቸውን የጠበቁና የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያላለፈ መሆን አለበት።

፲/ የማህበረሰብ ተፋሰስ አልሚዎች ተፈጥሯዊ የግብርና ግብዓቶችን እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።

## ክፍል ሦስት

## ስለማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኅበር አመሠራረት

### ፲. ስለ ህብረት ሥራ ማኅበር አመሠራረት

፩/ የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በክፍል ሦስት የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፪/ መሠረታዊ ማኅበሩ በማህበረሰብ ተፋሰሱ ስፋት ወይም ወሰን መሠረት መቋቋም አለበት። ሆኖም ግን የማህበረሰብ ተፋሰሱና የአስተዳደር ወሰኖች የሚለያዩ ከሆነ ማኅበሩ የወረዳውን ወሰን ተከትሎ መቋቋም አለበት፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

7/ Si looga hortago dhaawac soo saamayn kara o dhaqashada shinida, midhaha, iyo bay'ada oo ay sababto isticmaalka kiimikada cayayaanku, waaxda loo xilsaaray qaybinta kiimikooyinkaasi waa in ay si waafi ah wacyi galin u siisaa isticmaalayaasha aanay bartaa in ay isticmaalaan kiimikooyinka xilli iyo wakhti ku haboon maalintii intaanay ku buufin, shinilayda waa in la war galiyaa si ay taxadarka ku haboon uga qaataan.

8/ Iyadoon la ismoodsiinayn sida uu qabo fakhrada (3) ee qodobkan, isticmaalka kiimikooyinka qaar maadaama ay dabiici ahaan sun yihiinn aanay ku keeni karaan dhibaato xoogan dhirta iyo bay'ada, waa in la isticmaalaa iyadoo caawimaad iyo kormeer soke laga helayo khabiirada taxadar ku haboona laga qaataa si aan loogu qubin qashinkooda wabiyada,barkadaha,laagaha iyo il-biyood oo kasta.

9/ Gashiyada lagu isticmaalo aagaga biyo-rogyada waa in ay waafaqaan heerka loo baahan yahayn aanay noqdaan kuwo aan dhicin.

10/ Isticmaalayaasha biyo-rogyada waxaa lagu dhiiri galinayaa in ay isticmaalaan gashiyada beeraha ee dabiiciga ah.

## QAYBTA 3AAD

## AAS_AASIDA ISKAASHATOOYINKA BULSHADA EE AH ISTICMAALAYAASHA BIYO-ROGYADA BULSHADA

### 10. Aas_Aasida Iskaashatooyinka Bulshada Ee Ah Isticmaalayaasha Biyo-Rogyada Bulshada

1/ Iyadoon la ismoodsiinayn sida uu qabo bayaanka iskaashatooyinka bulshadu, waa in lagu dhaqmaa sida uu qabto qaybtan 3aad.

2/ Iskaashada waa in lagu aas-aasaa iyadoo lagu salaynayo baaxada iyo xuduuda biyo-roga bulshada. Hase ahaatee, marka xuduuda biyo-roga bulshada iyo ta maamulku aanay is waafiqin, iskaashatada waa in laga aas-aasaa xuduuda dagmada. Shuruuc gaar ah waa in lagu ilaaliyaa.

፫/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ዩኒየኖች የዞን አስተዳደር ወሰንን ተከትለው የሚደራጁ ሲሆን በዞን ውስጥ በተመሳሳይ ተግባር ከአንድ በላይ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ዩኒየን ሊኖር አይችልም፡፡

3/ Midowga iskaashatooyinka isticmaala biyo rogga bulshada waa in lagu aas-aasaa iyadoo la raacayo xuduuda maamulka gobolka; Wixii isku ojeedo ah, kaliya hal midow baa la aas-aasi.

፬/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ፌደሬሽኖች የክልል ወሰንን ተከትለው የሚደራጁ ሲሆን በክልል ውስጥ በተመሳሳይ ተግባር ከአንድ በላይ ሊኖር አይችልም፡፡

4/ Federayshanka iskaashatooyinka isticmaala biyo rogga waa in lagu aas-aasaa iyadoo la raacayo xuduuda maamulka deegaanka, Wixii isku ojeedo ah, kaliya hal federayshan baa la aas-aasi.

፭/ እንደአስፈላጊነቱ በአገር ደረጃ አንድ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ፌደሬሽን ሊደራጅ ይችላል፡፡

5/ Federayshanka qaranka ee iskaashatooyinka isticmaala biyo rogyada bulshada ayaa laga yaabaa in la aas-aaso, markay lagamamaarmaan noqoto.

፮/ የማኅበሩ መመስረቻና መተዳደሪያ ደንብ ተፋሰሱን በባለቤትነት ይዘው እንዴት እንደሚያለሙት ፣ እንደሚያስተዳድሩት ፣ እንደሚጠብቁትና እንደሚጠቀሙበት በዝርዝር የሚደነግግ ሆኖ ተጠቃሚ ማህበረሰቡ የመከረበትና ስምምነት ላይ የደረሰበት መሆን አለበት።

6/ Isfahamka ururada iyo qodobada ururada waa in ay falanqeeyaan kuna heshiiyaan isticmaalayaasha bulshadu waana in uu ka koobnaado qodobo qeexan oo ah siday ay bulshad u yeelanayso biyo-rogga si dareen lahaansho leh na horumariyaan, maareeyaan, ilaaliyaan oo ay isticmaalaan.

፯/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኅበር አስፈላጊ መመዘኛ መስፈርቶችን አሟልቶ በመቅረብ በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ መሠረት አግባብ ካለው ባለሥልጣን ሕጋዊ ሰውነት ያገኛል።

7/ iskaashatooyinka isticmaala biyo rogga bulshadu waa in, marka ay buuxiyaan shuruudaha laga rabo, ka helaan shati ganacsi xafiiska ay khusayso.

፰/ ከተፋሰሱ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶች እንደ ሣር፣ ደን እና የደን ውጤቶች ወይም መሰል የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶች በዓይነትም ሆነ በገንዘብ ተሸጠው ከተገኘው ገንዘብ ላይ ለአባላት የሚከፋፈልና ለተፋሰሱ ልማት ዓላማ በማኅበሩ ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ የሚሆነው የገንዘብ መጠን በማኅበሩ የውስጥ ደንብ ይወሰናል።

8/ Marka waxsoo-saarka khayraadka dbiiciga ee meelaha biya-rogyada bulshadu haysato sida cawska, kaymaha, waxsoo-saarka kaymaha ama waxsoo-saarada kale lagu iibiyo mood ama maal, xadiga lacagta ah waxaa qaybsanaya xubnaha ururada bulshada lacagta lagu dhigo bangiga magaca ururada horumarinta biyo-rogyadana waa in uu qeexaa xeer hoosaadka ururku.

## ፲፩. ሰለተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማህበር አባላት

## 11. Xubnaha Ururka Isticmaalayaasha Biyo-Rogyada

ከሚከተሉት መስፈርቶች አንዱን የሚያሟሉ ኢትዮጵያውያን በዚህ አዋጅ መሠረት የተፋሰስ ተጠቃሚዎችህብረት ሥራ ማህበር አባል ለመሆን መብት አላቸው፡-

Muwaadiniinta itoobiya ee buuxiya mid ka mid ah shuruudahan soo socdaa, wuxuu xaq u leeeyahay in ka mid noqdo iskaashatooyinka biyo-rogyada bulshada sida uu qabo bayaanku.

፩/ በተፋሰሱ ክልል ውስጥ የመሬት ይዞታ ያላቸውና ከዚሁ በሚገኝ ገቢ የሚተዳደሩ፣

፪/ በተፋሰሱ ክልል ውስጥ የመሬት ይዞታ ባይኖራቸውም በዙሪያው ነዋሪዎች ከመሆናቸው የተነሣ ከተፈጥሮ ሀብቱ ተጠቃሚዎች የሆኑ ወገኖች፤

፫/ ኗሪነታቸው በተፋሰሱ ክልል ውስጥ ባይሆንም መሬት ተከራይተውም ሆነ በሌላ ህጋዊ መንገድ ከተፋሰሱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች።

፬/ በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ የተደነገገው ቢኖርም በማህበረሰብ ተፋሰስ በተፋሰስ ክልሉ ውስጥ የመሬት ይዞታ ያላቸውና ዕድሜያቸው ከ፲፰ ዓመት በታች የሆኑ ሰዎች በሞግዚቶቻቸው አማካኝነት በአባልነት ሊመዘገቡ ይችላሉ።

፭/ በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን መስፈርቶች አሟልተው የተገኙ ልዩ ትኩረት የሚያሻቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የህብረት ሥራ ማህበሩ አባል የመሆንና ማኅበሩ የሚያስገኛቸውን ጥቅሞች ተካፋይ የመሆን ሙሉ መብት አላቸው።

## ፲፪. ስለማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማኅበር የክብር አባላት

፩/ የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማኅበር ለዓላማው ተፈፃሚነት የሚያግዙ ሆነው በተፋሰሱ አካባቢ የሚንቀሳቀሱ ነገር ግን የተፋሰሱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ያልሆኑትን ግለሰቦች፣ ድርጅቶች ወይም ተቋማት በክብር አባልነት ሊቀበል ይችላል።

፪/ የክብር አባላት በተፋሰሱ ተጠቃሚዎች ማኅበር ውስጥ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ ወይም በማናቸውም ጉዳይ ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም።

## ፲፫. የክብር አባላት ሚና እና ኃላፊነት

፩/ የክብር አባላቱ በራሳቸው ተነሳሽነት ወይም በማኅበሩ ሥራ አስፈጻሚ ጥያቄ ስለተፈጥሮ ሀብቱ ልማትና ጥበቃ ትምህርትና ምክር ይለግሳሉ፣ እንደዚሁም የቴክኒክ፣ የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

1/ Kuwa dhul kahaysta biyo-rogga ku noolaa halkaa.

2/ Shakhsiyaadka, xataa hadaanay dhulka haysan aaga biyo-roga, se isticmaala khayraadka dabiiciga maadaama ay dagan yihiin biyo-rogga dhexdiisa ama aaggiisa.

3/ Shakhsiyaadka aan ku noolayn biyo-roga aagiisa laakiin hadana si uun ugu xidhan biyo-rogga sida dhul ka kiraysi ama si kale oo sharci ah.

4/ Si ka duwan sida bayaanku qabo, shakhsiyaadka dhul ku leh biyo-rogga laakiin ka yar da'da sideed iyo toban jir waxaa loo diwaan galin cida masuulka ka ah.

5/ Dhamaan dadka baahiyaha gaarkaa leh ee buuxiyey shuruudaha bayaankani dajiyey waxay xaq u leeyhihiin in ay ka mid noqdaan xubnaha iskaashatooyinka deedna ay ka faa'iidaystaan.

## 12. Xubno sharafeedka Ururka Isticmaalayaasha Biyo-Rogyada bulshada

1/ Ururka isticmaalayaasha biyo-rogyadu waxaa laga yaabaa in ay aqbalaan xubno sharafaeed; shakhsiyaad, Haayado,ama xafiisyo kuwaasoo ka taageera gaadhitaanka ujeedooyinkooda kana shaqeeya aagga biyo-rogga xataa hadaanayba si toos ah uga faa'iidaysan biyo-rogga.

2/ xubno sharafaeedku kuma laha xuquuq in ay wax doortaan ama la doorto amaba ay codeeyaan sinaba marka la dooranayo ururka isticmaalayaasha biyo-rogyada.

## 13. Doorka iyo Masuuliyadda Xubnaha Ururka

1/xubno sharafaeedku waa in ay si iskood ah ama ku salaysan codsiga gudiga maamulka ururka, ay bixiyaan aqoon iyo talo ku saabsan horumarinta khayraadka dabiiciga ah, ilaalintiisa aanay bixiyaan taageero farsamo iyo maaliyadeed.

፪/ የክብር አባላቱ በተፋሰሱ ሥራ አመራር ኮሚቴ በሚቀርብላቸው ጥሪ መሠረት በጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባዎች እንዲሳተፉ በማድረግ ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡

**፲፬. የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኀበር አባላት መብት**

በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማህበር አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳፫ እና ፳፬ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በማህበረሰብ ተፋሰስ ውሰጥ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች በጋራ ወይም በግል የመጠቀም፤

፪/ በማህበሩ ሥር አባላት እንደሙያቸውም ሆነ ፍላጎታቸው የተጠቃሚዎች ቡድን በመፍጠር ተፋሰሱን በማይጎዳ ሁኔታ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ የመሰማራት፤

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎች እንደ ንብ ማነብ፣ ወተትና የወተት ተዋፅኦ ማቀነባበር እና ማቅረብ፣ እንስሳት ማድለብ፣ እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች ማምረት እና ማቅረብ፣ አትክልት እና ፍራፍሬ ማምረትና ማቅረብ እንዲሁም አንደ መኖ ልማት ያሉ የተፋሰስ ልማቱን የማይጎዱ ሥራዎችን ያጠቃልላል፤

፬/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም ላይ የግንዛቤ ዕውቀት በሚያስጨብጡ መድረኮች የመሳተፍ፡፡

**፲፭. የማህበሩ አባል ያልሆኑ የማህበረሰብ ተፋሰሱ ተጠቃሚዎች መብቶች**

፩/ በማህበረሰብ ተፋሰሱ ውስጥ በግል ወይም በማህበረሰቡ ወይም በህጋዊ አካል በተረጋገጠ የወል ይዞታ ላይ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች የመጠቀም፤

፪/ አባል ለመሆን የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ካሟሉ በማንኛውም ጊዜ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማህበር አባል የመሆን፤

2/ Marka ay u yeedhaan gudiga maamulka biyo-roggu, waxay ka qayb gali karaan shirarka guud oo ayna ka fikir dhiiban karaan.

**14. Xuquuqaha xubnaha iskaashatooyinka isticmaala biyo-rogga.**

Iyadoon la ismoodsiinayn sida uu qabo bayaanka iskaashatooyinka bulshadu, qof kasta oo ka mid ah iskaashatooyinka isticmaala biyo-roggu waa in uu yeeshaa xuquuqahan soo socda;

1/ Isagoon waxyeelaynayn sida uu qabo qodobka 23 iyo 24 ee bayaankan, wuxuu xaq u leeyahay in uu isticmaalo khayraadka biyo-rogga si shakhsi ah iyo is wada jir ahba;

2/ In uu sameeyo howlo nolol soo-saar isagoo ka hoos abuuraya iskaashatada kooxo isticmaalayaal, isagoon wax yeelaynayn biyo-rogga.

3/ Howlaha nolol soosaarka ah ee lagu sheegay fakhrada (2) ee qodobkan, waxaa ka mid ah shini-dhaqasho, habaynta iyo soosaarka caanaha iyo waxsoo-saarka caanaha , habaynta iyo soosaarka bay'ada, khudarada iyo midhaha, horumarinta calafka kaasoon wax yeelaynayn horumarinta biyo-rogga.

4/ Ka qayb-qaadashada shirarka wacyi galinta iyo cilmi korodhsiga ku saabsan ilaalinta, horumarinta iyo ka faa' iidaysiga biyo-rogyada.

**15. Xuquuqaha kuwa aan xubnaha ahayn iskaashatooyinka isticmaala biyo-rogga.**

1/ Isticmaalka khayraadka dabiiciga ah si gaa ah ama si guud ama dhulka lawada leeyahay si sharci ah oo ay xaqiijisay cida ka masuuli.

2/ Marka ay buuxiyaan shuruudaha ka mid ahaanshaha, in ay noqdaan xubno ka mid aha iskaashatoyiinka isticmaalayaasha biyo-rogyada bulshada xiligay doonaan.

፫/ የማህበረሰብ ተፋሰስን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም በሚመለከት ግንዛቤና ዕውቀት በሚያስጨብጡ መድረኮች ላይ የመሳተፍ፤

፬/ ማህበሩ ከተፋሰሱ ልማት ጋር በተያያዘ በሚያከናውኗቸው ተግባራት ምክንያት በግል ይዞታ ላይ ከሚከሰት ጉዳት የመጠበቅ፡፡

**፲፮. የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኅበር አባላት ግዴታዎች**

የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኅበር አባል የሆነ ማንኛውም ሰው በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ የተደነገጉ ግዴታዎች እንደአግባብነታቸው መፈፀማቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፦

፩/ በተፋሰሱ ውስጥ በሚካሄድ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ላይ የመሳተፍ፣

፪/ በተፋሰሱ ክልል ያሉትን ተፈጥሯዊና በልማት የተገኙ ሀብቶች ከውድመት የመጠበቅና የመከላከል፣

፫/ በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚወሰን የአባልነት ክፍያ የመክፈል፣

፬/ በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በግል፣ በቡድንና በአጠቃላይ በሚከናወኑ የውይይት፣ የዕቅድ ዝግጅት፣ የጥበቃና የልማት ተግባራት ላይ የኑሮ ሁኔታቸውን በማይጎዳ መልኩ የጉልበት አስተዋጽኦ ማድረግን ጨምሮ በንቃት የመሳተፍ፣

፭/ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ልዩ ልዩ የተፈጥሮ ሀብት ልማት መሠረተ ልማቶች፣ ተጠግነው የዘወትር ጥቅም መስጠታቸውን እንዲቀጥሉ ማኅበሩ በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት በጥገና ሥራ ላይ የመሰማራት።

፮/ አባል ባልሆኑ የግል ባለይዞታዎች መሬት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ተግባራት አለማከናወን፡፡

**፲፯. የማህበሩ አባል ያልሆኑ የማህበረሰብ ተፋሰሱ ተጠቃሚዎች ግዴታዎች**

፩/ በወል ይዞታ ላይ ተጠቃሚ ለመሆን የልማትና የጥበቃ ተግባር ላይ ከማህበር አባላት እኩል ተሳትፎ የማድረግ፤

3/ Ka qayb-qaadashada shirarka wacyi galinta iyo cilmi korodhsiga ku saabsan ilaalinta, horumarinta iyo ka faa’ iidaysiga biyo-rogyada.

4/ Ka ilaalinta dhulka ay gaarka haystaan waxyeelada kasoo gaadhi karta howlaha biyo-rog horumarineed ee ururada.

16. Waajibaadka xubnaha iskaashada isticmaalayasha biyo-rogyada bulshda.

Qof kasta oo ka mid ah iskaashada isticmaalayaasha biyo-rogu, iyadoon laga talaabasanayn sida uu qabo bayaanka ururada iskaashatooyinku, mutatis

mutandis, wuxuu leeyahay waajibaadyadan soo socda;

1/ In uu ka qayb qaato horumarinta khayraadka dabiiciga ah ee laga samaynayo biyo-rogga.

2/ In uu ilaaliyo oo uu ka difaaco burbruinta khayraadka sida dabiiciga ah lagu helay iyo kuwa lagu helay howlaha horumarinta ee biyo rogga;

3/ In uu bixiyo qaadhaanka ka mid ahaanshaha sida ay qabaan qodobada u yaal ururku.

4/ In uu si fir fircoon uga qayb qaato shirarka, diyaarinta qorsheyaasha iyo howlaha horumarinta sida in u ku deeqo shaqaale, isagoon wax yeelaynayn nolosha shaqaalaha, howlaha si gaar ah, si koox ah ama si wada jir ah iyadoo loo eegayo qodobada u yaal ururka.

5/ In uu wax ka qabto dayactirka kaabayaasha horumarinta khayraadka dabiiciga ah ee u baahan dayactir si waafaqsan mudaynta ay soo saaraan ururku si uu u bixiyo adeeg joogta ah.

6/ In uu ka dhowrtoomo qabashada howlaha wax-yeelayn kara dhulka ay haystaan dadka aan ururka ku jirin.

17. Waajibaadka ka faa’iidaystayaasha aan xubnaha ka ahayn iskaashatooyinka isticmaala biyo-rogyada bulshada.

1/Si ay uga faa’iidaystaan dhulka lwada leeyahay , in ay ka qayb galaaan howlaha ilaalinta iyo horumarinta si la mid ah sida xubnaha iskaashatooyinka.

፪/ የማህበረሰብ ተፋሰስን ሊጎዱ የሚችሉ ተግባራትን ከመፈፀም መቆጠብ፤

፫/ በግል ይዞታቸው ላይ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም የተፋሰሱን ደህንነት የሚጎዱና የተፈጥሮ ሀብት መራቆትን የሚያስከትሉ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ፤

፬/ በተፋሰሱና በአካባቢው በሚገኝ የደን ሀብት ላይ እሳትና መሰል አደጋ በሚከሰት ጊዜ ማህበሩ ለሚያደርገው የልማትና የጥበቃ እንቅስቃሴ የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

## ፲፰. ከአባልነት ስለመሰናበት

የማህበረሰብ ተፋሰስ አባል የሆነ ሰው በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፩ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በጊዜ ሂደት ሳያሟላ ቀርቶ ሲገኝ ከአባልነት ይሰናበታል፡፡

## ፲፱. የማኅበሩ አደረጃጀት

ማኅበሩ ከዚህ በታች የተገለፀው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

፩/ የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ፣

፪/ የሥራ አመራር ኮሚቴ፣

፫/ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች።

## ፳. ማኅበሩ ከሌሎች አካላት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

፩/ ከቀበሌ አስተዳደሩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በመፍጠር አስፈላጊውን ድጋፍ ማግኘት ይችላል።

፪/ በአካባቢው ከሚንቀሳቀሱም ሆነ ከሌሎች መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወይም ማኅበራት ጋር የማኅበሩን ዓላማ እውን ለማድረግ የሚያግዙ ስምምነቶችን ሊያደርግ ይችላል።

፫/ አንድን ውስን ሥራ በክፍያ ወይም ያለክፍያ ለማከናወን ከተለያዩ አካላት ጋር ሊዋዋል ይችላል።

2/ In ay ka dhowrsadaan qabashada howlaha wax yeelayn kara biyo-rogga bulshada.

3/ Taxadar u isticmaalka khayraadka dabiciga ah ee ay gaarka u haystaan si aanu isticmaalkaasi u wax yeelayn bad-qabka biyo-rogga iyo burburka khayraad dabiiciga ah ee biyo-rogga.

4/ Marka dab ama shil kale ku dhaco kaymaha biyo-roga iyo aagagiisa, in ay la shaqeeyaan iskaashatada sidii u xakamayn lahaayeen dhibka iyo howlaha dib-uhorumarinta.

## 18 Waayidda xubinimada

Iyadoon laga boodayn isticmaalka sida uu qabo bayaanka iskaashatooyinka bulshadu, qofka ka midka ah iskaashatada biyo-rogyada bulshada waa laga caydhin karaa xubinimadiisa marka uu/ay ku fashilmo in uu fuliyo shuruudaha lagu qeexay qodobka 11 ee bayaanka.

## 19. Qaab-dhismeedka ururka

Ururka isticmaalayaasha biyo-roggu waa in uu yeeshaa waaxahan soosocda:

1/ Shir guud
2/ Gudi fullin
3/ Gudi-hoosaad, marka loo baahdo.

## 20. Xidhiidhka ururku la leeyahay waaxaha kale.

1/ Waxaa laga yaabaa in ay ka helaan taageero iyagoo la aas-aasaya xidhiidh toos ah maamulka qabalaha;

2/ Waxaa laga yaabaa in ay heshiisyo lagalaan dawlada ama haayadaha ama ururada ka shaqeeya deegaanka amaba cid kale oo ka saacida xaqiijinta ujeedooyinkooda;

3/ Waxaaba laga yaabaa in ay qandaraas la sexeexdaan waaxyo kala duwan si ay u qabtaan shaqo gaar ah lacag halagu qaato ama yaan lagu qaadane;

ክፍል አራት

የማህበረሰብ ተፋሰስ ጥበቃ፣አስተዳደርና አጠቃቀም

፳፩. የተፋሰስ ልማት ሥራዎች አጠባበቅ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም

፩/ የገጠር መሬት ባለይዞታ መብቶችና ግዴታዎችን አስመልክቶ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም በተፋሰስ ውስጥ የሚገኝ የግል ወይም የወል ባለይዞታ እንደ መሬቱ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ የአፈርና ውኃ መጠበቂያ ሥራዎችን በመሥራትና በመንከባከብ እንዲሁም በመጠገን የአፈር ክለትን በመከላከል የአፈርን ለምነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት።

፪/ ማንኛውም የግል ወይም የወል ባለይዞታ፡-

ሀ) በተፋሰሱ ውስጥ በተሠሩ የልማት ሥራዎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ልቅ የእንስሳት ስምሪትን የመቆጣጠርና የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፤

ለ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙት የመሬት ይዞታዎቹ ዳር ድንበር፣ በማሳው ውስጥና በመንገዶች ዳር የደን፣ የመኖ ዛፎችንና አልሚ የእፅዋት ዝርያዎችን በመትከል፣ በመንከባከብና በመጠበቅ የአካባቢውን ለምነትና ጤንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፤

ሐ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙ የይዞታ መሬቶቹ አካባቢ ወንዞች፣ ሐይቆች፣ ምንጮች፣ ቦረቦር ስፍራዎችና ውኃ አዘል መሬቶች ያሉ እንደሆነ እነዚሁ በአጠቃቀምና በአያያዝ ሣቢያ ጉዳት እንዳይደርስባቸው እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በሚያወጣው ሕግ መሠረት በቂ የመከላከያ ርቀት የመተው ግዴታ አለበት፤

መ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኘው ይዞታው ላይ የሚፈጠር ትርፍ የጎርፍ ውኃ ቢያጋጥም ይኸው በሌሎች አጎራባች ማሳዎች ላይ ጉዳት እንዳያስከትል፣

QAYBTA 4AAD

ILAALINTA, MAARAYNTA, IYO KA FAA'IIDAYSIGA BIYO-ROGYADA BULSHADA

21. Ilaalinta, Maaraynta, Iyo Ka Faa'iidaysiga Howlaha Horumarinta Biyo-Rogyada

1/ Iyadoon lagu xadgudbayn sida ay qabaan shuruucda kale ee la xidhiidha xuquuqda iyo waajibaadka dadka ay haysta dhulka baadiyaha, dhulkasta oo gaar ah, ama dhulka lawada leeyahay ee ku yaala biyo-rog waa in, iyadoo lagu salaynayo qaab-dhismeedka dhulka, waajibaad ka saarnaadaa in ay qabtaan shaqooyin ilaalinta carada iyo biyaha, daryeelka iyo dayactirka si looga hortago carro guurka loona joogteeyo waxsoo-saarka carada.

2/ Dadka haysta dhulkasta oo gaar ah, ama lawada leeyahay waxaa waajib ku ah:

a) Ka celinta iyo ka ilaalinta xoolaha si looga hortago dhaawac soo gaadha howlaha horumarineed eel aga sameeyey biyo-rogga.

b) Joogtaynta caafimaad qabka iyo caro-samida carada iyagoo ku beeraya, ilaalinaya kaynta, geedaha calafka ah, iyo noocyada dhirta ee kor u qaada caro-samida geerasha beertiisa iyo dhinacyada la maro ee biyo-rogyada;

c) In uu u baneeyo, iyadoo la eegayo xaalada goobta, iyo shuruucda ay soo saarto cida ay khusaysaa, banaan kufilan oo u dhaxaysa dhulkiisa iyo wabiyada, dooxyada, jirarka ladayac tiray iyo goob-biyoodyada ku yaal hareeraha dhulkiisa si looga fogaado dhaawac soo gaadha marka uu isticmaalayo ama uu maaraynayo dhulkiisa.

d) In uu ku shubu biyaha saa'idka ah ee ka soo baxa beertiisa iyo kuwa kaga yimaada beeraha kale ee ka sareeya biyo shub dabiiciga ah ama la sameeyey si looga hortago dhib ay daadadku ku keenaan beeraha kale.

ከሌሎች የሚመጣውንም በማቀባበል ወደ ሰው ሠራሽ ወይም የተፈጥሮ መፋሰሻ ቦዮች እንዲፋሰስ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

ሠ) በተፋሰሱ ክልል ውስጥ የሚገኝ ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (መ) የተጣለውን ግዴታ ለመወጣት ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ያጋጠመው እንደሆነ ይህንኑ ለሚመለከተው የተፈጥሮ ሃብት ተቋምና ለማህበሩ ማሳወቅ አለበት፤

ረ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኘው የይዞታ መሬቱ ውስጥ ወይም ዳር ድንበሮች ላይ ያለማቸው ወይም የሚያለማቸው የደንና የእፀዋት ዝርያዎች በጥላቸውና በጠፈጠፋቸው ምክንያት የተጎራባቹን ባለይዞታ የሰብል ምርትና ሌሎች መብቶች የሚጎዳ መሆን የለበትም፤

ሰ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚመለከተው አካል የፀደቀ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በሚኖርበት ጊዜ መሬቱን በዕቅዱ መሠረት የማልማትና የመንከባከብ ግዴታ አለበት፤

ሸ) በተፋሰሱ ውስጥ የእሳት ቃጠሎ እንዳይነሳ አስፈላጊውን የጥንቃቄ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለበት፤

ቀ) ሰብሉን ለመጠበቅ ከሚያከናውናቸው ተግባራት በስተቀር በማህበረሰብ ተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙ ማሳዎቹና በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትና አዕዋፋት አካባቢውን ለቅቀው እንዳይሰደዱ ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

በ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙ የይዞታ መሬቶቹ ውስጥ ተክሎና ተንከባክቦ ያሳደጋቸውን የደን ዛፎች፣ የመኖና አልሚ የእፅዋት ዝርያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ህግና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች መሰረት ተግባራዊ መደረግ አለበት።

e) Si ka duwan sida uu qabo fakhrada(2) ee qodobkan, qofku waa in uu war galiyaa ururka iyo xafiiska khayraadka dabiiciga ah ee ay khusayso hadii dhibtu ka wayntahay awoodiisa.

f) Waa in uu ka ilaaliyaa beerta iyo xuquuda jaarkiisa dhibta ay keeni karto hadhka iyo biyaha geedaha ka baxa beeriisa amaba ijaarka dhulkiisa ku yaala biyo-roga.

g) Marka uu jiro qorshe dhul isticmaal oo ay ansixisay cida ay khusaysay ee biyo-rogu, waa in uu horumariyaa, ilaaliyaana dhulkiisa sida ku cad qorshaha;

h) waa in uu taxadar ku haboon yeeshaa sidii looga fogaan lahaa dab ka dhasha biyo-rogga;

i) Waa in uu ka taxadaraa barakicinta duurjoogta iyo shimbiraha ku nool beertiisa iyo dhulka ku wareegsan ee biyo-roga bulshda marka laga reebok aliya marka uu ka ilaashanayo xayawaankaas midhaha beertiisa;

j) Marka ay timaado isticmaalka kaynta, daaqa iyo dhirta kor u qaada caro-sanka ee uu kabeeray beertiisa ku taal biyo-rogga, sharciga Horumarinta kaymaha, ilaalinta iyo isticmaalka iyo shuruucda kale ee la xidhiidha waa in lagu isticmaalo.

## ፳፪. <u>ስለ እንጨት፣ እንጨት ያልሆኑ የደን ውጤቶች እና ሣር አጠቃቀም</u>

## 22. Isticmaalka xaabada, waxyaabaha aan kaynta ahayn iyo daaqa

፩/ በተፋሰሱ ክልል ውስጥ በግል ወይም በወል ይዞታዎች ላይ የመጠቀም መብት ያላቸው ሰዎች በእነዚህ ይዞታዎች ላይ ያለሙትን ወይም የተተከሉትን ደረቅ እንጨት፣ ዛፍ፣ ቁጥቋጦ፣ ሣር እና እንጨት ያልሆኑ የደን ውጤቶች የመጠቀም መብት አላቸው።

1/ Dadka xuquuqda isticmaal u haysta dhulka gaarka ama ka lawada leeyahay eek u yaala biyo-roga dhexdiisu waxay sidoo kale xaq u leeyihiin in ay isticmaalaan xaabada, qalalsan, geedaha, laamaha, daaqa iyo bey'ada (fooxa IWM) ee ka baxa ama laga beero dhulkaasa.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሱት ባለይዞታዎች ውጭ በተፋሰስ ክልል ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ደረቅ እንጨት፣ ዛፍ፣ ቁጥቋጦ፣ እንጨት ያልሆነ የደን ውጤት ወይም ሣር የማኅበሩ አባላት የጋራ ንብረት ስለሆነ፣ በማኅበሩ ውስጠ ደንብ መሠረት ማኅበሩ ቆርጦ፣ አጭዶና ሰብስቦ መጠቀም ይችላል።

2/ Xaabada qalalsan, geedaha, laamaha, daaqa iyo bey' ada(fooxa IWM) kasta ee aan ahayn kuwa kuyaal dhulkaa lagusoo sheegay fakhrada (1) ee qodobkan iyo kuwa kuyaala biyo-roga dhexdiissu waah hanti ay wada leeyihiin xubnuhu waanay jaran karaan una isticmaali karaan si sharci ah.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተጠቀሱት ሀብቶች አጠቃቀም አቅርቦቱን ዘላቂነት ባለው መንገድ ለመጠበቅ በሚያስችል አግባብ መፈፀም ይኖርበታል።

3/ Isticmaalka khayraadka lagusoo sheegay fakhrada (1) iyo (2) ee qodobkan, waa in loo isticmaalaa si aan wax yeelaynayn waaritaankooda.

## ፳፫. <u>በተፋሰሱ ክልል ውስጥ ስለሚገኝ ድንጋይና አሸዋ አጠቃቀም</u>

## 2323. Isticmaalka dhagaxa iyo niista dhulka biyo-rogga.

በማዕድን ሥራዎች አዋጅ መሠረት ቀድሞ ማዕድን በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላት መብትና ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ፦

Uyadoon la saamaynayn xuquuqda kuwii ka shaqaynayey sida ku cad bayaanka macdan qodista:

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ (፩) በተጠቀሱት ይዞታዎች ላይ የሚገኙት አሸዋ እና ድንጋይ የመጠበቅ እና የመጠቀም ኃላፊነት እና መብት አግባብነት ባለው የማዕድን ሥራዎች ህግ መሰረት የባለይዞታዎች ይሆናል፤

1/ Iyadoo loo eegayo shuruucda khusaysa macdanta, masuuliyada ilaalintooda iyo isticmaalka dhagaxa iyo niista ee laga helo dhulka lagu sheegay qodobka 25(1) ee bayaankan,Waxaa iska leh cida dhulka haysata;

፪/ በተፋሰሱ ክልል ውስጥ በታቀፈና የወል ወይም የመንግሥት ይዞታ በሆነ ሥፍራ ላይ የሚገኝ ድንጋይና አሸዋ አግባብነት ባለው የማዕድን ሥራዎች ህግ መሠረት ድንጋይና አሸዋውን ለተፋሰሱ ልማት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፤

2/ Dhagaxa iyo niista laga helo biyo-roga dhexdiisa iyo kuwa ku yaal dhulka lawada leeyahay ama dowladu leedahay, waxaa yeelanaya ururka waxaana loo isticmaali karaa horumarinta iyadoo la raacayo shuruucda macdanta ee khusaysa;

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች ቢኖሩም የድንጋይና አሸዋ አቅርቦቱን ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀምና ለመጠበቅ እንዲቻል የአፈር ክለትና የአካባቢ መጎዳት እንዳያስከትል ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

3/Si aan khilaafsanayn sida ku cad fakhradaha (1) iyo (2) ee qodobkan, si loo isticmaalo loona ilaaliyo dhagaxa iyo niista si hab waara leh, waa in taxadar loo yeeshaa si aan xaaluf loo keenin.

## ፳፬. በማህበረሰብ ተፋሰሱ ክልል ውስጥ ስለሚገኝ የውሃ ሀብት አጠቃቀም

በማህበረሰብ ተፋሰስ ክልል ውስጥ የሚገኘውን የውሃ ሃብት አጠቃቀም አግባብነት ያለው የውሃ ሃብት አስተዳደር ህግ በሚፈቅደው መሠረት የሚፈጸም ይሆናል::

## ፳፭. ስለ ሥርዓተ ምሕዳር አገልግሎት ክፍያ

፩/ የማህበረሰብ ተፋሰሱ በመልማቱ ምክንያት ተጠቃሚ የሆኑ አካላት ለማህበረሰቡ የተፋሰስ ልማት የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለባቸው።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ መሠረት የሚከፈል ከውሃ ጋር የተያያዘ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ በውሃ ሀብት አስተዳደር ሕግ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል

## ፳፮. የሥርዓተ ምሕዳር ጉዳት ካሣ

በመሠረተ ልማት ግንባታ ወይም በሌላ ምክንያት በማንኛውም ሁኔታ በተፋሰሱ ወይም በተፋሰስ ተጠቃሚዎች ላይ ጉዳት ያደረሱ አካላት ላደረሱት ጉዳት አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ተመጣጣኝ ካሣ መክፈልና አካባቢውን ተመጣጣኝ ወደ ሆነ ሥነ-ምህዳር የመመለስ ግዴታ አለባቸው።

## ክፍል አምስት

## የተፋሰስ ማኅበረሰቡን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች

## ፳፯. የተጠናቀቁ የተፋሰስ ሥራዎች ርክክብ

፩/ ማንኛውም የግል ወይም የወል ባለይዞታ በራሱ፣ በኅብረተሰቡ፣ በማኅበሩ ወይም ሥራውን አጠናቅቀው በሚያስረክቡ መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተከናወኑትን የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ቆጥሮ መረከብ አለበት።

፪/ ርክክብ ሲካሄድ የተሠሩ የልማት ሥራዎች ጥራታቸው የተጠበቀ ስለመሆኑ የሚመለከተው የወረዳ ተቋም ማረጋገጥ አለበት።

## 24. Isticmaalka khayraadka biyaha ee aaga biyo-rogyada

Isticmaalka khayraadka biyaha ee biyo-rogyada bulshada/yar-yar waa in uu ku salaysnaado shuruucda itoobiya ee khusaysa isticmaalka kharaadka biyaha iyo maamulkooda.

## 25. Bixinta adeegyada ba'ada

1/ Shakhsiyaadka ka faa'iidaysanaya hurumarinta biyo-rogyadu waa in ay masuuliyad kasaarnaato bixinta adeega ba'ada loo qabtay si loo horumariyo biyo-rogga bulshada.

2/ Bixinta adeegyada ba'ada la xidhiidha biyuha sida ku cad fakhrada (1) ee qodobkan waa in uu ku salaysnaado shuruucda itoobiya ee khusaysa isticmaalka kharaadka biyaha iyo maamulkooda.

## 26. Magdhowga wax-yeelaynta ba'ada

Hadii wax yeelo soo gaadho biyo-rogga ama isticmaalayaasha biyo-rogga sabab dhismo kaabayaal dhaqaale ama howlo kale, cidda ka masuulka ah waxyeelada ayey saran tahay in ay bixiyaan wax yeelada ay gaysteen aanay kusoo celiyaan ba'adda sideedii sida ku cad shuruucda khusaysa.

## QAYBTA 5AAD

## HOWLAHA KALE EE KHUSEEYA BIYO-ROGGA BULSHADA

## 27. Wareejinta shaqooyinka biyo-rogga ee dhamaaday

1/ Cidkasta oo haysata dhul gaar ah ama dhul lawada leeyahay, waa in ay la xisaabtanto aanay la wareegaan shaqooyinka horumarinta ee uu isaga, bulshada, urur ama howlaha huramirineed ee ay qabatay dawladu ama haayado ee lagu wareejiyey.

2/ Marka wareejintu dhacdo, xafiiska ay khusayso ee dagmadu waa in uu xaqiijiyaa in howlaha hurumarineed ee lawareejinayaa ay waafaqeen heerkii tayo ee larabay.

፳፰. <u>ስለማበረታቻ</u>

፩/ በተፋሰሱ ክልል ውስጥ በግልም ሆነ በወል የተሠሩ የአፈርና ውኃ ልማትና ጥበቃ ሥራዎችን እየጠገነ በአግባቡ በመንከባከብ በተፋሰስ ውስጥ የላቀ ውጤት ላስመዘገበ ባለይዞታ የዕውቅና እና ማበረታቻ ሽልማት የሚሰጥበትን ሥርዓት ወረዳው ይዘረጋል።

፪/ በወረዳው ውስጥ ካሉት ማኅበራት የተሻለ የተፋሰስ ልማት ሥራ ላከናወነ ማኅበር ወረዳው የዕውቅናና ማበረታቻ ሽልማት የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል።

፳፱. <u>ስለ ሥርዓተ-ፆታ እና ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች</u>

፩/ በማናቸውም የተፋሰስ አስተዳደርና አጠቃቀም ሂደት ሚዛናዊ የፆታ ስብጥር መኖር አለበት።

፪/ ሴቶችና ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጥቅም በሚያስገኙ በማናቸውም የተፋሰሱ ልማት ተግባራት ሁሉ አቅማቸውና ሙያቸው በሚፈቅደው መጠን እኩል የመሣተፍ እና ተጠቃሚ የመሆን መብት ይሰጣቸዋል።

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፴. <u>የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኃላፊነት</u>

፩/ አግባብነት ያላቸውን ተቋማት በማስተባበርና አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ በመስጠት ይህንን አዋጅ የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት።

፪/ በክልሎችና በፌደራል መካከል የተፋሰስ ልማት አስተዳደርና አጠቃቀም የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል።

28. Dhiirigalinta

1/ Nidaam aqoonsi iyo abaal marin waa in ay dagmadu u samaysaa shakhsiyaadka muujiya shaqo wanaaga dhowrida iyo ilaalinta carrada iyo hurumarinta biyaha iyo ilaalinta shaqooyinka si shakhsi ah ama si wadar ah loo qabtay.

2/ Nidaam aqọonsi iyo abaal marin waa in ay dagmadu u samaysaa ururada dagmada ee muujiyey shaqo wanaag dhanka horumarinta biyo-rogyada .

29. Jinsiga iyo dadka baahiyaha gaarkaa qaba

1/ Dheeli tirka jinsiga waa in la xaqiijiyaa nidaam kasta oo biyo-rog maarayn iyo isticmaalba.

2/ Haweenka iyo dadka baahiya gaarka qabaa waa in ay xaq u leeyhihiin in ay si siman uga qayb-galaan ugana faa'iidaystaan intii aqoodooda ah iyo ogolaanshaha fasaxyo, dhamaan howlaha hurumarinta biyo-rogyada faa'iidada leh.

## QAYBTA 6AAD

## MISCELLANEOUS PROVISIONS QODOBO DHEERI AH

30. Waajibaadyada wasaarada

1/ Wasaaradu waxay leedahaya masuuliyada fulinta bayaankan iyadoo isku dubaridaysa xafiisyada ku haboon siinaysana taageerada farsamo eel agama-maarmaanka ah.

2/ Wasaaradu waa in ay aas-aastaa hab ay warbixinta khusaysa hururmarinta biyo-rogyada , maarayntooda iyo isticmaalkooda isku waydaarsadaan deegaanada iyo fadaraalku.

## ፴፩. የክልሎች ኃላፊነት

፩/ ክልሎች ይህንን አዋጅና ሌሎች ከተፋሰስ አስተዳደርና አጠቃቀም እንዲሁም ከማኅበራት አመሠራረትና አደረጃጀት ጋር ግንኙነት ባላቸው ሕጎች ላይ ግንዛቤ የመፍጠርና ማኅበራት እንዲመሠረቱ የመቀስቀስና ሕጎቹን የማስፈፀም ኃላፊነት አለባቸው።

፪/ ይህንን አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጣውን ደንብ ተከትለው ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣሉ።

## ፴፪. የግብርና ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የግብርና ጽ/ቤት ከማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ጥበቃና አስተዳደር አኳያ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ተግባርና ኃላፊነቶች አሉት፡-

፩/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ዕቅድ ዝግጅትን ይደግፋል ፤ የተዘጋጁትንም መርምሮ ያጸድቃል፡፡

፪/ የተፋሰስ ልማት፣ አስተዳደርና አጠቃቀምን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይከታተላል፤

፫/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ማህበር አባላት የተጠቃሚዎች ቡድን በመመስረት ገቢ በሚያስገኙ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፬/ የዋና ተፋሰስ እና የማህበረሰብ ተፋሰስን ስፋት እንደ አካባቢው መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ መሰረት በማድረግ ይወስናል፡፡

፭/ ከሚመለከተው የህብረት ሥራ ማህበር አደራጅ መስሪያ ቤት ጋር በመተባበር የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማህበራት መሥራች ኮሚቴ እንዲደራጅ ያደርጋል፡፡

## 31. Waajibaadyada deegaanada

1/ Deegaanada waxay masuuliyad ka saarantahay, ku wacyigalinta bayaankan iyo shuruucda kale ee la xidhiidha maamulka iyo isticmaalka biyo-rogyada iyo sidoo kale aas-aaska iyo habaynta ururada iyo dhiiri galinta aas-aaska ururo iyo fulinta shuruucdaas.

2/ Deegaanadu waa in ay soo saaraan awaamiir ku salaysan bayaankan iyo xeerar lasoo saari doono si loo fuliyo bayaanka.

## 32. Waajibaadka xafiisyada beeraha ee ay khusayso

Marka laga hadlayo ilaalinta, horumarinta iyo maamulka biyo-rogyada bulshada, xafiiska beeruhu wuxuu leeyahay shaqooyinka iyo masuuliyadahan soo socda;

1/ Taageerida diyaarinta qorshaha maaraynta biyo-rogyada; ansixinta qorshaha fulineed ee bulshada

2/ Isku dubaridka, hagida, iyo kormeerida hurumarinta, maamulka iyo isticmaalka khayraadka biyo-rogyada.

3/ Taageerida, kormeerida iyo joogtaynta samaysanka kooxo isticmaalayaal ah si ay nolol uga helaan biyo-rogyada bulshada ee degmada ku yaala.

4/ Go'aaminta xajmiga biyo-rogyada waawayn iyo ku yaryar/bulshada iyagoo ku salaynaya xaalada qaab-dhismeeka dhulka.

5/ Iyagoo kala shaqaynaya xafiiska ka masuulka ah habaynta iskaashatooyin bulsho , waa in ay habeeyaan gudida aas-aasayaasha iskaatada isticmaalayaasha bulshada

**፴፫. የህብረት ሥራ ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት**

ህብረት ሥራ ማህበራትን ለማደራጀት ስልጣን የተሰጠው አካል ተግባርና ኃላፊነት በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ በተቀመጠው መሠረት ይሆናል፡፡

**33. Waajibaadka iyo masuuliyadaha wakaalada iskaashatooyinka**

Waajibaadyada iyo masuuliyadaha xafiiska loo xilsaaray in ay habeeyaan iskaashatooyinku waa in uu u fuliyaa sida ku cad bayaanka iskaashatooyinka bulshada.

**፴፬. ስለጥፋቶችና ቅጣት**

፩/ ከዚህ አዋጅ አተገባበር ጋር በተያያዘ ለሚፈፀሙ ወንጀሎች በወንጀል ሕጉና በሌሎች ሕጎች የተደነገጉ ቅጣቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፪/ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገጉ ግዴታዎችን አለመወጣት የሚያስከትሉትን አስተዳደራዊ ቅጣት ዝርዝር አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**34. Ganaaxa**

1/ Ganaaxyada lagu aqoonsaday xeerka ciqaabta iyo shuruucda kale ayaa la isticmaali hadii danbi la xidhiidha maaraynta biyo-rogyada bulshadu dhaco.

2/ Talaabooyin maamul oo xoojinaya fulinta bayaankan waa in ay go'aamiyaan cidda masuulka ka ah fulinta bayaankan.

**፴፭. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

፩/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተቋቋሙ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ማህበራት ይህ አዋጅ በፀደቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ የማህበረሰብ ተፋሰስ ህብረት ሥራ ማህበር ሆነው መመዝገብ አለባቸው፡፡

፪/ ቀደም ሲል በነበረው አሠራር የተቋቋመ የተፋሰስ ኮሚቴ የዚህን አዋጅ መውጣት ተከትሎ በሚቋቋመው ህብረት ሥራ ማኀበር ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እስከሚተካ ድረስ ተቀባይነት ይኖረዋል።

**35. Qodobada Kala Guurka**

1/Iskaashatooyinka isticmaalayaasha biyo-rogga ee la aas-aasay sharci galka bayaankan ka hor waa in loo diwaan galiyaa sikaashatooyin bulsho iyadoo lasiinayo hal sano oo ay isku habanaynayaan la jaan qaadida bayaankan.

2/ Guddida biyo-roga ee lagu aas-aasay hab dhaqankii hore waay sii shaqaynayaan ilaa inta lagu badalayo guddi maamul ee iskaashatada bulshada lagu aas-aasayo sharci galka bayaanka.

**፴፮. ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ያወጣል።

**36. Awoodda soosaarida Xeerarka**

Golaha wasiirada ayaa soo saari xeerarka fulinta bayaankan

**፴፯. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**37. Shuruucda aan khusayn**

Ma jiro sharci, xeer, awaamiir ama caado aan la jaan qaadayn sida ku cad bayaankan oo ku haboonaan karta arimaha bayaankani khuseeyo.

**፴፰. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳሕለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

38. Taariikhda dhaqan galka

Bayaankani waa in uu dhaqan galaa taariikhda lagu daabaco jaraa'idka ogaysiiska ee federaalka.

Waxaa lagu sameeyey Addis Ababa Maalintii 25aad ee bisha August 2020

SAHLEWORK ZEWDIE

MADAX WAYNAHA DAWLADA DIMUQRADIGA FEDERALKA ITOOBIYA